# በምርጫ ዋዜማ አማራጭን እንጂ

# ጫጫታን አንሻም !! (፩)

ዮናስ 12-04-14

የኢትዮጵያ ህዝቦች በተግባራዊ ምርጫ ወሳኝ የሥልጣን ምንጭና ባለቤቶች መሆናቸውን ያረጋገጡት በ1984 ዓ.ም ሚያዚያ ወር ላይ ተደርጎ በነበረው የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤቶች ምርጫ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የሽግግር መንግሥቱ ዓላማ አገሪቱ የምትመራበትን ህገ መንግሥት በህዝብ ተሳትፎ ማፅደቅና በህዝብ ምርጫ ለሚቋቋመው መንግሥት አስፈላጊውን ፖለቲካዊና ህጋዊ ቅድመ ሁኔታ ማሟላት በመሆኑ ኢህአዴግ ሰላሳ ሁለት ያህል በሰላም ለመታገልና ለመወዳደር የወሰኑ ድርጅቶችን ጋብዞ በጋራ የሽግግር መንግስት እንዲያቋቁሙ ካደረገ በኋላ የሽግግር መንግሥቱ የሚመራበት ፕሮግራም በሁሉም ተሳታፊ ፓርቲዎች ስምምነት ላይ የተደረሰበትና የጋራ አቋም ላይ የተመሰረተ መለስተኛ ፕሮግራም ወይም የሽግግሩ ወቅት ቻርተር ተብሎ የሚታወቀው ሰነድ ከተዘጋጀና ከፀደቀ በኋላ ነው፡፡

ይህ የመጀመሪያው ሊባል የሚቻለውና የኢትዮጵያ ህዝቦች በተግባራዊ ምርጫ ወሳኝ የስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆናቸውን ያረጋገጡበት የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤቶች ምርጫ ነው፡፡

ከዚህ፣ በህዝብ ምርጫ መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችል መደላድል በኋላ በ1986 ዓ.ም የተለያዩ ፓርቲዎችና የግል ተፎካካሪዎች የተወዳደሩበት የህገ መንግሥት ጉባኤ አባላት ምርጫ የተካሄደ ቢሆንም በህዝብ ምርጫ መንግሥት ለመመስረት የሚያስችል አገር አቀፍና ክልላዊ ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው ህገ መንግሥቱ ከፀደቀ በኋላ በግንቦት ወር 1987 ዓ.ም ላይ ነው፡፡

በአንድ አገር የተረጋጋ የዴሞክራሲ ሥርዓት ለማስፈን የሚቻለው ፓርቲዎች በሚገነባው ሥርዓት መሰረታዊ ባህሪያት በተለይም በህገ መንግሥቱ ይዘት ላይ ተስማምተው ሲያድሩ እንደሆነ ይታወቃል፤ የአለም ታሪክ አስተምህሮም የኸው ነው፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለው ግንኙነት ሰላማዊና በነፃ ውድድር ላይ፣ ወይም ደግሞ በመጠፋፋት  እና ግጭት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ የተረጋጋ ወይም በሁከት የሚናጥና ለአደጋ የተጋለጠ እንዲሆን የማድረግን ውጤት የሚያስከትል ነው፡፡

በአንድ በኩል ህገመንግሥታዊ ስርዓቱ ትክክለኛ በመሆኑ መቀጠል አለበት የሚሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱ በውድም በግድም መፍረስ አለበት የሚሉ ፈፅሞ የማይቀራረቡ አቋሞችን የያዙ ፓርቲዎች በሚኖሩበት አገር የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት እንደማይቻል የታወቀ ነው፡፡ በአንፃሩ፣ ሁሉም ፓርቲዎች ህገመንግሥታዊ ስርአቱን ተቀበለው በፖሊሲና ስትራቴጂ ደረጃ የሚታዩ የአማራጭ ልዩነታቸውን በሰላማዊ መንገድ የሚገልፁበት ሥርዓት ደግሞ በተረጋጋ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና በአገሮች ሰላማዊ ውስጣዊ ጉዞ እጅግ የተመቸ ሁኔታን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች  በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የላቀ ሚና መጫወት እንደሚችሉ እና መጫወትም እንደሚገባቸው ኢህአዴግ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡

 የአንድን የህብረተሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያሥችሉ አማራጭ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ እነዚህ ሃሳቦች በህብረተሰብ ክፍሉም ሆነ በአጠቃላይ በህዝቡ ተቀባይነት እንዲያገኙ በመጣር፣ ሃሳቦቹ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ በመታገል ከፍተኛ የአመራር ሚና መጫወት እንደሚችሉ እና በዚህ መልኩ የተደራጀ አመራር ሰጥተው የህዝብን ድጋፍ ካገኙ የመንግስት ሥልጣንን ይዘው ሃሳባቸውን ተግባራዊ በማድረግ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ አሥተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ ድርጅቱ ስለመቀበሉ  በድርጅታዊ ሰነዶቹ ላይ  ሁሉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ነገር ግን ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመጫወት የሚችሉት አመለካከታቸው፣ እምነታቸውና አሠራራቸው ዴሞክራሲያዊ ሲሆን ነው የሚለው ገዢው ፓርቲ፣ *የውስጥ አሰራሩ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ፓርቲ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባትና ማበብ ፋይዳ ያለው አስተዋፅኦ ማበርከት አይችልም* ሲልም ያሰምርበታል፡፡

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ አስተዋፅኦ እንዳለውና ተቋዋሚ ፓርቲዎችም ሁሌ የውዝግባቸው አንድ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡትን የሚዲያ አጠቃቀም በተመለከተም ገዢው ፓርቲ አገሪቱ በምትከተላቸው መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ተከታታይ ትንተናዎችንና በተለያዩ ወገኖች የሚቀርቡ የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦችን እያቀረበ የውይይትና የክርክር መድረክ ሆኖ ማገልገል እንዳለበት በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን፣ ሚዲያ ይህን የመሠለ በሳል የፖለቲካ ውይይትና ክርክር መድረክ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ሃሳቦችን በነፃ በማንሸራሸር የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ የሚረዳ መሆኑን አበክሮ ያምናል፡፡

በዚሁ መሠረት የአገራችን ፖለቲካ በድርድርና በውይይት የሚመራበትን ባህል ለማዳበርና የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ ቦታ እንዳይኖረው የሚያደርግ ህብረተሰባዊ ግንዛቤ መፍጠር እንደተቻለ የሚገልፀው ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሠጥቶ በመቀበል ዴሞክራሲያው ድርድርና ውይይት የሚመራና እየተመራ ያለ መሆኑንም ይናገራል፡፡ ብዙ ጊዜ በአንዳንድ ተቃዊሚዎች በኩል በአገራችን የተከናወኑ ምርጫዎችን ነፃና ፍትሃዊ ላለማድረግ በምሳሌነት የሚቀርበው ምርጫ 97 እስከ ድምጽ አሠጣጡ ድረስ የነበረው ሂደት ድፍን አለም ያደነቀው ነፃ፣ ፍታሃዊ አና ዴሞክራሲያዊ እንደነበር የሚያወሳው ኢህአዴግ *ከድምፅ አሰጣጡ ሂደት በኋላ የተከሰቱ መደማመጥና መነጋገር የጎደላቸው የሁከትና የአመፅ አካሄዶች የፈጠሩት ነውጥና ማህበራዊ መታወክ ምንጫቸው የጥላቻና የአመፅ ፅንፈኝነት ናቸው* ሲል ይከራከራል፡፡

እነዚሁ የጥላቻና የአመፅ ፅንፈኝነት ጎራ ውስጥ የሚመደቡት ተቃዋሚ ፓርቲዎች የፖለቲካ ምህዳርን በተመለከተ የሚያነሱት ክልሼ ጥያቄ ፍፁም መሰረተቢስና ውሃ የማያነሳ ጥያቄ መሆኑን የሚገልፀው ኢህአዴግ፤ ይህንንም ጥያቄ - “ከሽግግሩ ወቅት ቻርተር ጀምሮ የተመለሰ ጥያቄ ነው“ ሲል ይደመድማል - እሚሰማ የሌለ መሆኑን በመግለፅ። ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም እየተበራከቱ መምጣታቸውን፣ በርካታ ድምፆችና ሚዲያዎች መፈጠራችውን፣ የተለያዩ የግል ፕሬሶች መፍላታቸውን፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት ነገር ግን ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲጓዝ ህጋዊ መሠረት መጣሉን፣ የተቃዋሚዎች የመደመጥ መብትና በምክር ቤት ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የተካሄደውን የህግ ቀረፃና የማፅደቅ ሂደቶች፣ ከሰላም በላይ ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩ በህጋዊ መንገድ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ

ፓርቲዎችና የፖለቲካ ተዋናዮች የፈጠረውን ህጋዊ መደላድልና አመቺነት /የፓርላማ ህግ፣ የፓርቲዎች የምርጫ ማስፈፀሚያ ህግ፣ የጋራ ም/ቤት መቋቋም ወዘተ/ በማስታወስ በምህዳር ጉዳይ ላይ የሚነሳው ሁሉ መነሻውና ምንጩ ሌላና ፀረ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ስለ መሆኑም ኢህአዴግ ደረቱን ነፍቶ ይናገራል፡፡

ዘንድሮ፣ ሃገራችን ለ5ኛ ጊዜ ሃገር አቀፍ ምርጫ ልታካሂድ በዋዜማው ላይ ትገኛለች፡፡ ምርጫውን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ባወጣው ፕሮግራሙ መሰረት ለዚሁና ለ5ኛ ጊዜ ለሚከናወነው ሃገር አቀፍ ምርጫ 10 የሚሆኑ ፓርቲዎች የምርጫ ምልክታቸውን ስለመውሰዳቸው ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ አሳውቋል፡፡ ያም ሆኖ ግን ‹‹ማን እንደኛ ›› በማለት የሚታወቁቱ እና ‹‹ገዢው ፓርቲ ይፈራናል›› ሲሉ ሌት ተቀን የሚናገሩቱ ፓርቲዎች እስካሁን የምርጫ ምልክት አለመውሰዳቸውንም ሰምተናል፡፡

ጉዳዩ በምርጫ መወዳደር/አለመወዳደራቸው፣ ወይም የምርጫ ምልክት መውሰዳቸው/አለመውሰዳቸው አይደለም፤ ጉዳያችን ምርጫ በደረሰ ቁጥር በመርህ ደረጃ ተፎካከሪና አማራጭ ይሆናሉ ብለን የምንጠብቃቸው ፓርቲዎች መራጭ ለሆነው ህዝብ አማራጫቸውን ትተው መንጫጫታቸውን መቀጠላቸው ነው፡፡

የመጀመሪያዎቹን ሶስት ዙር ሃገር አቀፍ ምርጫዎች ሃገሪቱ ባካሄደችበት ጊዜ ከመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ተያይዞ በመራጩም ሆነ በፓርቲዎች በኩል የነበረው ግንዛቤ ገና ጀማሪ ነበርንና እምብዛም ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ አማራጮች ሳናገኝ በምርጫው ላይ ተሳትፎ ብናደርግም ቢያንስ የዜግነት ግዴታችንን በመወጣት ረገድ ሚናችንን ተጫውተናልና የአማራጭ ጉዳይ ብዙም አሳስቦን ያልነበረ መሆኑ ይታወሳል፡፡ ባያሳስበንም ጀማሪ ነንና አይገርመንም፡፡ ከ3ኛው ዙር ሃገር አቀፍ ምርጫ በኋላ ግን በመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ላይ የሁሉም ዜጋ ግንዛቤ ከፍ ያለ መሆኑን በተለያዩ አግባቦች ተረድተናልና አማራጭን መሻታችን ተገቢና ትክክል ከመሆኑም በላይ የፖለቲካና የፓርቲዎች መርህ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን በተለይም እራሳቸውን በፖለቲካው መድረክ ላይ ከፍ አድርገው ከሚቆልሉቱ ፓርቲዎች ባሳለፍናቸው 10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ አንዳችም አማራጭ ከመስማት ይልቅ መንጫጫታቸውን መስማት እንድንሰለቻቸው አድርጎናል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም እየተገዛለት ያለው የምርጫ ፖለቲካ ሥርዓት ከላይ የተመለከተው ሆኖ ሳለ ፓርቲዎች ሁሌም እንደ ፓርቲ ቆመው ፖለቲካን ሥራቸው ማድረግ ያቃታቸው መሆኑ ሳያንሰን፣ ቢያንስ በምርጫ ዋዜማ ብቅ ሲሉ እንኳ ከገዢው ፓርቲ ፕሮግራሞች ባሻገር ሃገራችንን እና ህዝቧን ከድህነት የሚያወጡና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚወሰዱ ናችው ያሏቸውን ፕሮግራሞች አቅርበው ለመራጩ እድል እንደመስጠት ገዢ ሥርዓቱን በማብጠልጠል የመጠመዳቸው ጉዳይ የገዢውን ፓርቲ ጥርጣሬ እና ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለውን እይታ እንጋራ ዘንዳ የሚያስገድደን ይሆናል፡፡ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ጋር ተያይዞ የነበረው የግንዛቤ እጥረት ቢያንስ ተቃሏል ባልንበት ምርጫ 97 ወቅት በምርጫው ብርቱ ተፎካካሪ ሆነው የነበሩት *ቅንጅት* እና *ህብረት* በስተመጨረሻ ይዘው የቀረቡት አማራጭ አማራጭ በመሰለ ፕሮግራም የተሸፋፈነ አመጽና ባዶ ስሜት ብቻ የነበረ መሆኑም ውሎ አድሮ የተገለጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ባዶ ስሜት መሆኑንም በስተኋላ ከተስተዋሉትና ከፓርቲዎች መርሆና ከፖለቲካ አመራሮች ስብእና ውጪ በሆኑት እሰጣ ገባዎች ማጠየቅ ይቻላል፡፡

በሦሥተኛው አገራዊ ምርጫ ወቅት ፋክክሩ፣ የድምፅ መሥጠትና የቆጠራ ሂደት ሁሉም በሠላም መጠናቀቁን ተከትሎ አሸናፊው ወገን ቢለይም ተቃዋሚው ሃይል በተለይም ቅንጅትና ህብረት አሁን ደግሞ መድረክ በሚባለው ፓርቲ ሥር የተጠለሉቱ ሃይሎች ውጤቱን በፀጋ ለመቀበል አልፈቀዱም፡፡ ውጤቱን በተመለከተ ሃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው አካል ባደረገው የማጣራት ስራ (በገዢውም ሆነ በተቃዋሚው በኩል የቀረቡ ታዛቢዎችን በማካተት) የተቃዋሚዎቹ የአሸንፈናል አዋጅ ተገቢነት እንደሌለውና ጥቂት በሚባሉ ቦታዎች ላይ ደግሞ ምርጫ እንዲደገም በመወሰኑ ቀድሞውኑም ቢሆን በአቋራጭ ሥልጣን የቋመጠው ሃይል ለህግ አልገዛም ባይነቱን ቀጥሎበት የነበረ መሆኑም ይታወሳል፡፡

እነዚህ አሁን በመድረክ ጥላ ሥር የሚገኙትና መኢአድ አንድነት ሰማያዊ በመባል የሚታወቁት ፓርቲዎች  በ3ኛው ምርጫ ክፍለ ጊዜ በቅንጅትና በህብረት ሥር የነበሩ ናቸው። እነዚህ ሃይሎች በወቅቱ በያዙት የዜሮ ድምር ፖለቲካ ቀጥለው አመፅ በመቀስቀስ ወደሥልጣን ለመምጣት ያላቸውን ውጥን እውን ለማድረግ፣ በቀን ቢያንሥ ከሦሥት ጊዜ በላይ የፕሬስ መግለጫ በመስጠት አመፁን ለማጋጋል ያላሰለሰ ጥረት ማድረጋቸውን

አንዘነጋም ፡፡ በጊዜው የነበረውን የግሉን ፕሬስና የቅንጅት(ቶች)ን *ያልተቀደሰ ጋብቻ* (የወቅቱ የፖለቶካ ተንታኞች ሲገልፁት እንደነበረው) የ97ቱ የኢህአዴግ የምርጫ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ "አብዶ ማሳበድ የሚያውቀው የኢትዮጵያ የግል ፕሬስ የቅንጅትን የጧትና ማታ መግለጫዎች በሰፊው ያራግባል፡፡" ሲሉ መግለፃቸውንም ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት  የግል ፕሬሱና ተቃዋሚው ድህረ ምርጫ 97 ከህግ የበላይነት በላይ በመሆን ህግንና ህገወጥነትን በማጣቀስ የተቋማትን ህጋዊና ሉአላዊ ስልጣን ከመጋፋት ጀምሮ ገዢው ፓርቲንም ሆነ መንግሥት አልፎም የባለሥልጣናትን የግል ጉዳይ ሳይቀር በማንሳትና ጮሀው በማጯጯህ ሃገሪቷን ለትርምስ፣ ወንበሩን ለራሳቸው  ቢመኙም በአለም አቀፍ ደረጃ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ ወደጎን ተገፍቶ የሰለጠነ የውይይትና የድርድር ባህል ወሳኝ ቦታ እየያዘ መምጣቱን በተገነዘበው ህዝብና ባስገነዘበው መንግሥት፣ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ፣ ምርጫን የአመፅ መሳሪያ ማድረግና በምርጫ ሰበብ ሁከት መቀስቀስ ፀረዴሞክራሲያዊነትና ዘመን ያለፈበት ፈሊጥ መሆኑን በተገነዘበው ህዝብ አማካኝነት ምኞታቸው ሁሉ  ከሽፎ ጉዞ (ምርጫቸው ሆነና) ወደ ቃሊቲ አቀና፡፡

የነውጠኛው አመራር በይቅርታ ከተፈታ በኋላ ገሚሱ በይፋ የአሸባሪ ቡድን አደራጅቶ ሲንቀሳቀስ ገሚሱ ደግሞ ላመለጠችው  ወንበርና ዋንጫ እንደገና ለመፋለም ግንባር ፈጥሮ *መድረክ* በሚል መለያ ቢንቀሳቀስም ነገሩ ያደቆነ ሰይጣን ሆነና አሁንም እንደገና ህገወጥነትን እያጣቀሱ መቀጠልንና ምርጫውን ገና ከዋዜማው ማጠልሸት ጀመሩ፡፡ በዚሁ የውግዘትና የአመጽ ፓለቲካ በቅንጅት ደቁነው በመድረክ የቀሰሱት ሃይሎች የምርጫ 2002  የመራጮች ምዝገባና ቅስቀሳ ሳይጀምር "ካሸነፍን ትክክል ነው ከተሸነፍን ግን ተጭበርብሯል" የሚል ፌሽካቸውን ነፍተው የነበረ መሆኑም ይታወሳል፡፡

የዜሮ ድምር ስብስቡ ከላይ በተገለፀው መልክ ምርጫ 97 ላይ በዜሮ ቢሸነፍም በተለይም የስብስቡ አደራጅ የሆኑት አንዳንድ አለም አቀፍ ድርጅቶችና በነፃ ፕሬስ ስም የተቋቋሙ ሃገር በቀል ጋዜጦች ከምርጫ 2002 ወደኋላ ሁለት ዓመት ቀደም ብለው *መድረክ* የተባለ ጠንካራና የብዙ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነ ፓርቲ መወለዱን በይፋ ማወጃቸውና ማራገባቸውም ይታወሳል። *መድረክ* የተባለው ፓርቲ ከወዴት እነዳለና አመጣጡም ከወዴት እንደሆነ ሳይታወቅ ቢቆይም  በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ የተለመደውንና

በምርጫ 97 በዜሮ የተሸነፈበትን የቅንጅት አጀንዳ ይዞ ብቅ በማለት መገለጡም እንደዚሁ፡፡

ሆኖም ይህ ፓርቲና ስብስቡ ልክ እንደ ምርጫ 97ቱ ቅንጅት ቅጥ አምባሩ የጠፋና የሚያስተሳስርና አንድ የሚያደርገው ቀጭን ገመድ እንኳ የሌለው መሆኑ ገና ከመነሻው ግልፅ ነበር፡፡ ይህንንም አቶ በረከት በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ እንዲህ ያወጉታል" አንዱ ሶሻል ዴሞክራቲክ ነኝ ይላል፤ ሌላው ደግሞ ሊበራል ዲሞክራት ነኝ ይላል፤ አንዱ የኦሮሞ ህዝብ በቁመቱና በወርዱ ልክ መብቱ አልተከበረለትም ይላል፡፤ ሌላው ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት ለብሔር ብሔረሰቦች ከልክ በላይ መብት ሰጥቶ አገሪቱን ሊያፈራርሳት ነው ይላል፡፡ አንዱ የሚናገረውን ሌላው ያፈርሰዋል፡፡ ደግሞ እንደገና ሌላው ያፈረሰውን አንዱ ሊገነባ ይውተረተራል፡፡ ከኦሮሚያ ፈልቀናል የሚሉት ዶ/ር መራራ፡ አቶ ቡልቻ እና ዶ/ር ነጋሶ የሶስት የተለያዩ ድርጅቶች ባለቤት ሆነው ስለመድረክ ጥንካሬ ያወራሉ፡፡ --" እንደ አቶ በረከት አገላለፅ ተቃዋሚዎቻችን እንኳን ተቀናጅተው አገር ሊመሩ ይቅርና እራሳቸውም (እ'ስ-በ'ሳቸው) ያልተቀናጁ፤ ዱባ እና ቅሎች ነበሩ ማለት ነው፤ ዛሬስ? ለውጥ ይኖራል ብሎ መጠበቅ ቢከብድም መቸኮል አያስፈልግም (ከስህተት መማር ያለ ከመሆኑ አንፃር)ና እስኪ እናያቸዋለን።

ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን አሁን እየተያያዙት ያለው ሁኔታ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን የመያያዝ አዝማሚያ ሳይሆን፤ በመንግስትና በህዝብ ቁርጠኝነት በቁጥጥር ስር የዋለውን የድህረ ምርጫ 97 አመፅን ለመድገም ያለመ ሴራ መሆኑን በመገንዘብና እነሱም በዛ ወቅት የጠፋው ሰውና ንብረት መጥፋት የሌለበት መሆኑን በመገንዘብ የጋራና ሁሉንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊያግባባ የሚችል የፓለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ማዘጋጀት እንዳለበት በኢህአዴህ በኩል ጥሪ የቀረበ ሲሆን፤ እንደተፈራውም ሌሎቹ ፓርቲዎች አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እና የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች በማገናዘብ የስነምግባር ደንብና የምርጫ ስነምግባር ማዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ በማመን ወደድርድሩ ገብተው የተስማሙበትን ሰነድ አዘጋጅተው በማፅደቅ ወደሥራ ቢገቡበትም መድረክ የተባለው ፓርቲ ውልደቱ ከቅንጅት በመሆኑ እምቢኝ ባይነቱን አሁን ድረስ የገፋበት መሆኑን ከተነሳንበት ርእሰ ጉዳይ አንጻር ያጤኗል፡፡

እንዳሰበውም ምርጫው ገና ሳይደረግ "ተጭበርብሯል" ከማለቱም ባሻገር በምርጫው ተሳትፎ ገና ድምፅ የመስጠቱ ሂደት ሳይጋመስ በቀትር ሰዓት ላይ እንዳቸው *ተጭበርብራል* ሲሉ ሌላኛቸው ደግሞ የአሸንፈናል አዋጅ አስነገሩ፡፡

የሆነ ሆኖ አሁንም መነሻቸው የዜሮ ነበርና ከፍልሚያው በዝረራ ቢወገዱም አሁንም ለቀጣዩ ምርጫ ቅጣምባራቸው የጠፋባቸውና ምንም የውልና የትስስር መስመር የሌላቸው ፓርቲዎችን በመሰብሰብ ከወዲሁ እና ከዋዜማው ቀጣዩ ምርጫ የሁከትና የትርምስ ይሆን ዘንድ በመልፋት ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ለሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፋይዳ የሌለው ተራ የፖለቲካ ቁማር ነው፡፡ ተመሳሳይነቱና መድረክን ጨምሮ አንድነት መኢአድና ሰማያዊ የተሰኙት ፓርቲዎች የአቋራጭ ስልጣን ፈላጊ መሆናቸውን የሚያሳብቀው አሁንም በየጊዜውና ምርጫ በደረሰ ቁጥር የፖለቲካ አማራጮች ከማቅረብ ባሻገር በተምታቱ መግለጫዎች የተጥለቀለቁ መሆናቸውና ይህንኑም የነፃውን ፕሬስ ታፔላ የለጠፉ ጋዜጦች ማራገባቸውን አጠናክረው የቀጠሉበት መሆኑ ነው፡፡ ከአስረጂዎቻችን ጋር የተለመደውን ሰሞነኛ ጫጫታ አክለን በክፍል ሁለት ትርክታችን እንቀጥላለን፡፡